# የገቢዎች ሚኒስቴር
# መመሪያ ቁጥር 5/1996

## <u>የግብር እና ታክስ አስተዳደራዊ</u>
## <u>መቀጫዎችን ለማንሣት የወጣ መመሪያ</u>

ሚያዝያ 1996 ዓ.ም.
ገቢዎች ሚኒስቴር



Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

## የገቢዎች ሚኒስቴር

## መመሪያ ቁጥር 5/1996

### የግብር እና የታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ለማንሣት የወጣ መመሪያ

የታክስ ባለሥልጣኑ የግብር/የታክስ ግዴታቸውን በአግባቡ በሕግ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የማይወጡ ግብር/ታክስ ከፋዮችን ሀብት በመያዝና በመሸጥ ግብሩን/ታክሱን ለማስገባት የሚያስችለው ሥልጣን የተሰጠውና ስልት የተቀየሰለት ቢሆንም ግብር/ታክስ ከፋዮች በልዩ ልዩ ምክንያቶች ግዴታቸውን በሕግ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሳይወጡ ጊዜው ሊያልፍባቸው የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት እንዲሁም ጊዜው ካለፈ በኋላ ለመክፈል ቢፈቅዱም የአስተዳደራዊ ቅጣቱ ካልተቃለለላቸው የመክፈል አቅማቸው የተዳከመ ሊሆን እንደሚችል በመገንዘብ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን በሙሉ ወይም በከፊል ማንሳት ግብር ከፋዮች ህልውናቸው እንዲቀጥል የሚያግዝና ውዝፍ ፍሬግብር/ታክስም የበለጠ ሳይዘገይ ለመሰብሰብ አጋዥነት ያለው መሆኑ ስለታመነበት፣

ወጥ በሆነ ሁኔታ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበትን መስፈርት በማውጣት አድሏዊ አሠራርን ማስቀረት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በመጋቢት 1994 የወጣውና እስከ 1994 ላለው የግብር ዘመን የሚፈለገውን ግብር/ታክስ በተመለከተ ሲሰራበት የቆየው የመቀጫ አነሣሥ መመሪያ በአዳዲሶቹ አዋጆች በተሻሩት የግብር ሕጎች ላይ የተመሠረተ በመሆኑና አዲስ በወጡት አዋጆች ከሚጣሉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ጋር በተጣጣመ አዲስ መመሪያ የቀድሞውን መተካት በማስፈለጉ፣

የገቢዎች ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት የፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 57/89 አንቀጽ9/2/፣ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 106፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 42፣ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/95 አንቀጽ 20፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 አንቀጽ 17 መሠረት በግብር ወይም በታክስ ከፋዩ ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ ስለሚነሣበት ሁኔታ መመሪያ ለማውጣት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Records and Documentation

# <u>ክፍል 1 ጠቅላላ</u>

## አንቀጽ 1. *<u>አጭር ርዕስ</u>*

ይህ መመሪያ "የግብር እና የታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ለማንሣት የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 5/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## አንቀጽ 2. *<u>ትርጓሜ</u>*

1. "አስተዳደራዊ ቅጣት ወይም መቀጫ " ማለት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94፣ በተርንአቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/95፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 እና በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/90 ድንጋጌዎች መሠረት የግብር ግዴታን በአግባቡ ባለመወጣት የሚጣል የገንዘብ መቀጫ፣ ወይም የንግድ ፈቃድ የማሣገድ ወይም የማሠረዝ እርምጃ ማለት ነው::

2. "የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 104 በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 40፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 አንቀጽ 15 እና በተርን አቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/95 አንቀጽ 18 መሠረት የሚቋቋም ኮሚቴ ሲሆን ከላይ በተገለጡት አዋጆች መሠረት የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች እንዲነሱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በመቀበልና በመመርመር ለታክስ ባለሥልጣኑ ዋና ስራ አስኪያጅ ወይም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ የውሣኔ ሃሳብ የሚያቀርብ ነው::

## አንቀጽ 3. *<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>*

ይህ መመሪያ በፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን እንዲሰበሰቡ በተመደቡ የግብር /ታክስ/ ዓይነቶች ላይ የሚጣሉ አስተዳዳራዊ ቅጣቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል:: ሆኖም እስከ 1994 ዓ.ም. ድረስ ቀደም ሲል በነበሩ ሕጎች መሠረት የውዝፍ ግብር ግዴታ ላይ የሚጣሉና የሚሰበሰቡ መቀጫዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

የገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል
Ministry of Revenue
Records and Documentation Section

## ክፍል ሁለት

## አስተዳደራዊ ቅጣቶች ስለሚነሱባቸው ሁኔታዎች

### አንቀጽ 4. ወለድ አስተዳደራዊ ቅጣት ስላልሆነበት ወይም ስለሆነበት ሁኔታ

1. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 መሠረት በዘገየ የግብር ክፍያ ላይ የሚታሰበው ወለድ አስተዳደራዊ መቀጫ ባለመሆኑ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም:: ስለሆነም በዚህ መመሪያ በገቢ ግብር አዋጅ የተጣለ መቀጫ ሊነሳለት የሚችለው ፍሬግብሩን ወለድ ካለ ከነወለዱ አጠናቆ ከፍሎ ሲገኝ ብቻ ነው::

2. ወለድ አስተዳዳራዊ ቅጣት በሆነባቸው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ.285/94፣ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁ.307/95 እና የተርንኦቨር ታክስ አዋጅ ቁ. 308/95 ለሚከፈል ታክስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 6 በተመለከቱት ሁኔታዎች መቀጫዎች በሙሉ ወይም በከፊል የሚነሱት ታክሱ እና የወለድ ቅጣት ካለ ከነወለድ የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው::

### አንቀጽ 5. መቀጫዎች ሙሉ በሙሉ የሚነሱባቸው ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደራዊ መቀጫዎች ሙሉ በሙሉ የሚነሱት:-

1. ግብር ከፋዩ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገቢውን ወይም ታክሱን አስታውቆ ባስታወቀው መሠረት ግብሩን ወይም ታክሱን ወዲያውኑ የከፈለ ሆኖ በግብር ባለሥልጣኑ ግብር ወይም ታክሱ ሲወሰን (የገቢ ግብሩን በተመለከተ በልዩነት የሚፈለግበት የግብር መጠን በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 87 (2) ከፍተኛ ልዩነት ከሚባለው በታች ሲሆን) እና ይህንኑ በልዩነት የሚፈለግበትን ፍሬግብር ወይም ታክስ የውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (ሠላሣ) ቀናት ውስጥ አጠናቆ ከፍሎ ሲገኝ ፣

2. በመቀጠር የሚገኝ ገቢያቸውን እያሳወቁ የሥራ ግብር እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸው ተቀጣሪዎች ገቢያቸውን ራሣቸው አስታውቀው የሚፈለ

Ministry of Rev...
Records and Documentation Service

ግባቸውን ግብር ከከፈሉ ወይም የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው በ30 (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ ፍሬ ግብሩን አጠናቀው ከፍለው ከተገኙ፣

3. በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 35 እንደተመለከተው ግብር ከሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ጋር በማይገናኝ አኳኋን ንብረት አልፎ አልፎ በማከራየት ገቢ ያገኘ ሰው በዚህ ዓይነት ያገኘውን የዓመት ጠቅላላ ገቢ ራሱ አሳውቆ ግብሩን የከፈለ ወይም የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30(ሠላሣ) ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን ከፍሎ ከተገኘ ፤

4. በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 93 በተመለከተው መሠረት የገቢ ማስታወቂያው ከመመርመሩ በፊት ግብር ከፋዩ በራሱ ተነሣሽነት ወደ ተሳሰተ የግብር ውሣኔ እና አፈፃፀም ሊያመሩ የሚችሉ ስህተቶችን ያረመ እንደሆነ በገቢ ግብር አዋጁ የተጣለበት አስተዳደራዊ መቀጫ፤

5. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቀጥር 285/94 አንቀጽ 33 (1) እንደተመለከተው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ከተመዘገበ ሰው የገዛ ሰው በፈጸመው የማጭበርበር ተግባር ወይም ያልሆነውን እንደሆነ አድርጐ በመቅረቡ ምክንያት የተመዘገበው ሰው በስህተት ግብይቱ ከታክስ ነጻ እንደሆነ ወይም በዜሮ የማስከፈያ ልክ እንደሚከፈልበት አድርጐ የወሰደ እንደሆነ እና የታክሱ ባለሥልጣን ታክሱን ፡ ወለዱን እና መቀጫውን የተመዘገበው ሰው እንዲከፍል የውሣኔ ማስታወቂያ ሰጥቶት በ30(ሠላሣ) ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ፡

6. በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 መሠረት የቴምብር ቀረጥ ግዴታውን ራሱ አስታውቆ ፍሬግብሩን አጠናቆ ከከፈለ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ የቴምብር ቀረጥ ውሣኔ ማስታወቂያ ደርሶት በ21(ሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ ቀረጡን አጠናቆ ከፍሎ ሲገኝ ይሆናል።

## አንቀጽ 6. <u>መቀጫዎች በከፊል የሚነሱባቸው ሁኔታዎች</u>

በቁጥር 06/አ3/3/1 መጋቢት 8 ቀን 1996 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 86 ገቢን ባለማስታወቅ ወይም ዘግይቶ በማስታወቅ የተጣለው መቀጫ ስለሚነሳበት

የገቢዎች ሚኒስቴር መዝገብና ዶክመንቴሽን ክፍል
Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

ሁኔታ ለመወሰን የተላለፈው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ሁኔታዎች አስተዳደራዊ መቀጫዎች በከፊል ሊነሱ ይችላል::

1. ግብር ከፋዩ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገቢውን አስታውቆ ግብሩን የከፈለ ሆኖ በታክስ ባለሥልጣኑ ግብሩ ሲወሰን በልዩነት የሚፈለግበት ግብር በገቢ ማስታወቂያ ላይ መታየት ካለበት ግብር ከ25% ወይም ከብር 20000.00 ከሁለቱ ከአነስተኛው የበለጠ እንደሆነ እና የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሣኔ በደረሰው በ30 ቀናት ወስጥ በልዩነት የሚፈለግበትን ፍሬግብር አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ከመቀጫው 90%(ዘጠና ፐርሰንት) ይነሳል::

2. <u>ግብር ከፋዩ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገቢውን ወይም ታክሱን አስታውቆ ባስታወቀው መሠረት ግብሩን ወይም ታክሱን የከፈለ ቢሆንም የታክስ ባለሥልጣኑ ግብሩን ወይም ታክሱን ሲወስን በልዩነት የሚፈለግበትን ግብር ወይም ታክስ በተመለከተ የውሣኔ ማስታወቂያ ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሣኔ ደርሶት:-</u> (አዘግይቶ በመክፈል የተጣለው መቀጫ አነሣሥ የሚመለከተው የገቢ ግብር አዋጅን ብቻ ሲሆን መዝገብ ባለመያዝ የተጣለው መቀጫ አነሳስ ደግሞ የሚመለከተው የገቢ ግብርን እና የተጨማሪ እሴት ታክስን ብቻ ነው::)

   ሀ. በታክስ ባለሥልጣኑ ከ6 ወራት ሳይበልጥ በሚሰጠው የክፍያ ጊዜ ፍሬግብሩን አጠናቆ ከከፈለ በዚሁ ግብር/ታክስ ላይ አሳንሶ በማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈል እንዲሁም መዝገብ ያልያዘ ከሆነ መዝገብ ባለመያዝ የተጣለው መቀጫ 85%(ሰማንያ አምስት በመቶ) ይነሳለታል::

   ለ. ይግባኝ አቅርቦ በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ወይም አቤቱታም ሆነ ይግባኝ ያላቀረበ ከሆነ ሀብቱን የመያዝ ማስጠንቀቂያ በተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን አጠናቆ ከከፈለ በዚሁ ግብር/ታክስ ላይ አሳንሶ በማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈል እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ የተጣለው መቀጫ 80% (ሰማንያ በመቶ) ይነሳለታል::

   ሐ. በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ መሠረት ግብሩን/ ታክሱን እንዲከፍል ማስታወቂያ በተሰጠ በ30/ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን አጠናቆ ከከፈለ በዚሁ ግብር/ታክስ ላይ አሳንሶ በማስታወቅ አዘግይቶ በመክፈል

እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 75% (ሰባ አምስት በመቶ) ይነሳለታል::

መ. በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ በተሰጠበት ጉዳይ ሀብቱን የመያዝ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ በዚሁ ግብር/ታክስ ላይ አሳንሶ በማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈል እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 70% (ሰባ በመቶ) ይነሳለታል::

ሠ. ሀብቱን የመያዝ ትዕዛዝ በደረሰው ወይም ሀብቱ በተያዘበት ጊዜ ፍሬግብሩን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ በዚሁ ግብር/ታክስ ላይ አሳንሶ በማስታወቅ አዘግይቶ በመክፈል እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 65% (ስድሳ አምስት በመቶ) ይነሳለታል::

ረ. ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ነገር ግን የሐራጅ ወይም የጨረታ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት ፍሬግብሩን እና ሀብቱን ለመያዝ የወጡ ወጪዎችን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ በዚሁ ግብር/ታክስ ላይ አሳንሶ በማስታወቅ ዘግይቶ በመክፈል እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 60% (ስልሳ በመቶ) ይነሳለታል::

ሰ. ሀብቱ በታክስ ባለሥልጣኑ በሐራጅ ወይም በጨረታ ከመሸጡ በፊት ፍሬግብሩን እና ሃብቱን ለመያዝ የተደረጉ ወጪዎችን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ በዚሁ ግብር/ ታክስ ላይ አሳንሶ በማስታወቅ ዘግይቶ በመክፈል፣ እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 55%(ሃምሳ አምስት በመቶ) ይነሳለታል::

3. _ግብር ከፋዩ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገቢውን ወይም ታክሱን ሳያስታውቅ የቀረ ወይም የዘገየ ሆኖ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ደርሶት፡-_

ሀ. በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬ ግብሩን/ታክሱን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ባለማስታወቅ አዘግይቶ በመክፈል እና መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለበት መቀጫ 80%(ሰማንያ በመቶ) ይነሳለታል::

ለ. በታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ከ 3 ወራት ያልበለጠ የክፍያ ጊዜ ውስጥ ፍሬግብሩን/ታክሱን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ባለማስታወቅ ከተጣለበት

መቀጫ፣ ዘግይቶ በተከፈለ ግብር/ታክስ ላይ ከተጣለ መቀጫ እንዲሁም መዝገብ /ሠነድ ባለመያዝ ከተጣለበት መቀጫ 75% (ሰባ አምስት በመቶ) ይነሳለታል::

ሐ. ይግባኝ አቅርቦ በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ ከመሰጠቱ በ ፊት ወይም ይግባኝ ያላቀረበ ሆኖ ሀብቱን የመያዝ ማስጠንቀቂያ በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን/ታክሱን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ባለማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈልና መዘገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 70%(ሰባ በመቶ) ይነሳለታል::

መ. በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ መሠረት ግብሩን/ታክሱን እንዲከፍል ማስታወቂያ በተሰጠው 30 ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን/ታክሱን አጠናቆ ከከፈለ ባለማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈልና መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለበት መቀጫ 65% (ስድሳ አምስት በመቶ) ይነሳለታል::

ሠ. በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ በተሰጠበት ጉዳይ ሀብቱን የመያዝ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን/ታክሱን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ባለማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈልና መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 60%(ስልሳ በመቶ) ይነሳለታል::

ረ. ሀብቱን የመያዝ ትዕዛዝ በደረሰው ወይም ሀብቱ በተያዘበት ጊዜ የከፈለ እንደሆነ ባለማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈልና መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለበት መቀጫ 55%(ሃምሳ አምስት በመቶ) ይነሳለታል።

ሰ. ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ነገር ግን የሐራጅ ወይም የጨረታ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት ፍሬግብሩን/ታክሱን እና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ባለማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈልና መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 50%(ሃምሳ በመቶ) ይነሳለታል::

ሸ. ሀብቱ በታክስ ባለሥልጣኑ በሐራጅ ወይም በጨረታ ከመሸጡ በፊት ፍሬግብሩን/ታክሱን እና ሃብቱን ለመያዝ የተደረጉ ወጪዎችን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ባለማስታወቅ፣ አዘግይቶ በመክፈልና መዝገብ ባለመያዝ ከተጣለው መቀጫ 45% (አርባ አምስት በመቶ) ይነሳለታል::

Ministry of Revenue
Records and Documentation Section

4. <u>ግብር ከፋዩ የያዘው የሂሣብ መዝገብ በታክስ ባለሥልጣኑ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ግብር/ታክሱ በግምት የሚወሰን ሲሆንና የግብር/የታክስ ልዩነት ሲኖር፦</u>

ሀ. በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገቢውን ወይም ታክሱን አስታውቆ ባስታወቀው መሠረት ግብሩን/ታክሱን የከፈለ ከሆነ የመቀጫው አነሳስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/2/ በተመለከተው መሠረት ይሆናል::

ለ. በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገቢውን ወይም ታክሱን ሳያስታውቅ የቀረ ወይም የዘገየ ከሆነ የመቀጫው አነሳስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/3/ መሠረት ይሆናል::

5. <u>ግብር ከፋዩ የሂሣብ መዝገብ ባለመያዙ ግብሩ/ታክሱ በግምት ተወስኖበትና የውሣኔ ማስታወቂያ ደርሶት፦</u>

ሀ. በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገቢውን ወይም ታክሱን አስታውቆ ባስታወቀው መሠረት ግብሩን/ታክሱን የከፈለ ከሆነ በታክስ ባለሥልጣኑ የግብር/የታክስ ውሣኔ ልዩነቱን በተመለከተ ግብሩን አሳንሶ በማስታወቅና ዘግይቶ በመክፈል እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ የተጣለበት መቀጫ አነሳስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/2/ መሠረት ይሆናል::

ለ. በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገቢውን ወይም ታክሱን ሳያስታወቅ የቀረ ወይም የዘገየ ከሆነ ባለማስታወቅና ዘግይቶ በመክፈል እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ የተጣለበት መቀጫ አነሳስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/3/ መሠረት ይሆናል::

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ግብር/ታክስ ከፋዩ የውሣኔ ማስታወቂያ ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሣኔ ከደረሰው በኋላ ተገቢውን የሂሳብ መዝገብና ሰነድ ባለመያዙ የንግድ ፈቃዱ እንዲታገድ የተደረገበት እንደሆነ የሂሣብ መዝገብና ሰነድ ለመያዝ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸቱን ያረጋገጠና ለታክስ ባለሥልጣኑ መዝገብ እንደሚይዝና እንደሚያቀርብ ግዴታ የገባና



Ministry ... Records and Doc...

ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ የንግድ ፈቃዱ እገዳ እንዲነሳለት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይፃፍለታል።

6. <u>*በመቀጠር የሚገኝ ገቢውን እያሳወቀ የሥራ ግብር እንዲከፍል የሚጠበቅበት ተቀጣሪ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሣኔ ደርሶት፡-*</u>

ሀ. ይግባኝ አቅርቦ በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ወይም ይግባኝ ያላቀረበ ሆኖ ሀብቱን የመያዝ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 90%(ዘጠና በመቶ) ይነሳለታል።

ለ. በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ መሠረት ግብሩን እንዲከፍል ማስታወቂያ በተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬግብሩን አጠናቆ ከከፈለ የመቀጫው 80% (ሰማንያ በመቶ) ይነሳለታል።

ሐ. በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ በተሰጠበት ጉዳይ ሀብት የመያዝ ማስጠንቀቂያ በተሰጠ በ30/ሰላሳ/ ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም ከታክስ ባለሥልጣኑ ከ6 ወራት ሳይበልጥ በሚሰጥ የክፍያ ጊዜ ፍሬግብሩን አጠናቆ ከከፈለ የመቀጫው 70% (ሰባ በመቶ) ይነሳለታል።

መ. ሀብቱን የመያዝ ትዕዛዝ በደረሰው ወይም ሀብቱ በተያዘ ጊዜ ፍሬግብሩን እና ሀብቱን ለመያዝ የተደረገውን ወጪ አጠናቆ የከፈለ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ከ 2 ወራት ያልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፍሬግብሩን እና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 60%(ስድሳ በመቶ) ይነሳለታል።

ሠ. ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ነገር ግን የሐራጅ ወይም የጨረታ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት ፍሬግብሩን እና ሀብቱን ለመያዝ የተደረገውን ወጪ አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 50%(ሃምሳ በመቶ) ይነሳለታል።

ረ. ሀብቱ ከተያዘ በኋላ በሐራጅ/በጨረታ ከመሸጡ በፊት ፍሬግብሩን እና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 40%(አርባ በመቶ) ይነሳለታል።



Ministry ... Records and Documentation ...

7. <u>ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሆኖ ሳይመዘገብ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የፈፀመ ታክሱ በግምት ተወስኖ የውሣኔ ማስታወቂያ ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሣኔ ደርሶት፡-</u>

ሀ. በደረሰው በ30/ሠላሳ/ ቀናት ውስጥ ታክሱን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 50%(ሃምሳ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ለ. ይግባኝ አቅርቦ በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ወይም ይግባኝ ያላቀረበ ሆኖ ሀብቱን የመያዝ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ታክሱን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 45%(አርባ አምስት በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ሐ. በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ መሠረት ታክሱን እንዲከፍል ማስታወቂያ በተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ ታክሱን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 40%(አርባ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

መ. ይግባኝ ለጉባዔው ቀርቦ በተወሰነበት ጉዳይ ሀብቱን የመያዝ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ታክሱን የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 35% (ሰላሳ አምስት በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ሠ. ሀብቱን የመያዝ ትዕዛዝ በደረሰው/ሀብቱ በተያዘበት ጊዜ ታክሱን እንዲሁም ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 30%(ሰላሳ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ረ. ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ነገር ግን የሐራጅ ወይም የጨረታ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት ታክሱን እና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 25%(ሃያ አምስት በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ሰ. የተያዘው ሀብት በሐራጅ/በጨረታ ከመሸጡ በፊት ታክሱን፣ እና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 20%(ሃያ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

8. <u>*የግብር ከፋዩ ሀብት በእጁ የሚገኝ 3ኛ ሰው ሀብቱን እንዲያስረክብ ሀብት የመያዝ ትዕዛዝ ደርሶት ያለበቂ ምክንያት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ እንዲያዝ ታዞ በእጁ በሚገኘው የግብር ባለዕዳው ሀብት መጠን በግሉ ተጠያቂ ስለሆነ ይህንኑ እንዲከፍል የውሳኔ ማስታወቂያ ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ደርሶት፡-*</u>

ሀ. በ30 ቀናት ውስጥ የግብር ዕዳውን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከተጣለበት መቀጫ 70%(ሰባ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ለ. ይግባኝ አቅርቦ በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ወይም ይግባኝ ያላቀረበ ሆኖ ሀብቱን የመያዝ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የግብር ዕዳውን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከተጣለው መቀጫ 60%(ስድሳ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ሐ. በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ መሠረት የግብር ዕዳውን እና መቀጫውን እንዲከፍል ማስታወቂያ በተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ የግብር ዕዳውን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከተጣለበት መቀጫ 50% (ሃምሳ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

መ. ለግብር ዕዳው አከፋፈል ሀብት የመያዝ ማስጠንቀቂያ ደርሶት በ30 ቀናት ውስጥ የግብር ዕዳውን የከፈለ እንደሆነ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከተጣለበት መቀጫ 40%(አርባ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ሠ. ለግብር ዕዳው አከፋፈል ሀብት የመያዝ ትዕዛዝ በደረሰው ወይም ሀብቱ በተያዘ ጊዜ የግብር ዕዳውን የከፈለ እንደሆነ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከተጣለበት መቀጫ 30%(ሰላሳ በመቶ) ይነሳለታል፡፡

ረ. ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ነገር ግን የሐራጅ ወይም የጨረታ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት የግብር ዕዳውንና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የከፈለ እንደሆነ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከተጣለበት መቀጫ 20%(ሃያበመቶ) ይነሳለታል፡፡

ሰ. ሀብቱ ተይዞ በሐራጅ/በጨረታ ከመሸጡ በፊት የግብር ዕዳውን እና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የከፈለ እንደሆነ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከተጣለበት መቀጫ 10%(አስር በመቶ) ይነሳለታል፡፡

9. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር አለመቀነሱንና ወይም ገቢ አለመደረጉን ያወቀ ወይም ማወቅ የነበረበት ሥራ አስኪያጅ እና ግብሩ አለመቀነሱንና ወይም ገቢ አለመደረጉን ያወቀ ወይም ማወቅ የነበረበትና ሂሣቡን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነቱን በአግባቡ ያልተወጣ የሂሣብ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 90/4/ የተመለከተውን መቀጫ እንዲከፍል የውሣኔ ማስታወቂያ ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሣኔ ደርሶት:-

ሀ. በ30 ቀናት ውስጥ መቀጫውን አጠናቆ የሚከፍል የሆነ እንደሆነ የመቀጫው 80%(ሰማንያ በመቶ) ይነሳለታል::

ለ. ይግባኝ ለግብር ይግባኝ ጉባዔ አቅርቦ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት መቀጫውን አጠናቆ የሚከፍል የሆነ እንደሆነ የመቀጫው 70%(ሰባ በመቶ) ይነሳለታል::

ሐ. የግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ በሰጠ ወይም ሀብት የመያዝ ማስጠንቀቂያ በተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ መቀጫውን አጠናቆ የሚከፍል የሆነ እንደሆነ የመቀጫው 60%(ስድሳ በመቶ) ይነሳለታል::

መ. ሀብት የመያዝ ትዕዛዝ በተሰጠ ወይም ሀብቱ በተያዘበት ጊዜ መቀጫውን የሚከፍል የሆነ እንደሆነ የመቀጫው 50%(ሃምሳ በመቶ) ይነሳለታል::

ሠ. የተያዘው ሀብት የሚሸጥ ሆኖ የሐራጅ/የጨረታ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት መቀጫውንና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የሚከፍል የሆነ እንደሆነ የመቀጫው 40%(አርባ በመቶ) ይነሳለታል::

ረ. ሀብቱ በጨረታ/በሐራጅ ከመሸጡ በፊት መቀጫውንና ሀብቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የሚከፍል የሆነ እንደሆነ የመቀጫው 30%(ሰላሳ በመቶ) ይነሳለታል::

10. በታክስ ባለሥልጣኑ የቴምብር ቀረጥ ውሣኔ ማስታወቂያ ለቀረጥ ከፋዩ ደርሶት:-

ሀ. በታክስ ባለሥልጣኑ ከ3/ሶስት/ ወራት ወይም 90/ዘጠና/ቀናት ሳይበልጥ በሚሰጠው የክፍያ ጊዜ ቀረጡን አጠናቆ ከፍሎ ሲገኝ የመቀጫው 90% (ዘጠና በመቶ) ይነሳለታል::

በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ministry of Revenue
Records and Documentation Service

ለ. ቀረጥ ከፋዩ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርቦ በፍርድ ቤቱ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ቀረጡን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 80%(ሰማንያ በመቶ) ይነሳለታል።

ሐ. ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ የአፈፃፀም እርምጃ ከመቀጠሉ በፊት ቀረጡን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 70%(ሰባ በመቶ) ይነሳለታል።

መ. በፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሠረት በአፈፃፀሙ ሂደት መካከል ቀረጡን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 60%(ስድሳ በመቶ) ይነሳለታል።

ሠ. ሁለተኛ ይግባኝ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውን ይግባኝ ተመልክቶ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ሲቀርብና በሁለተኛ ይግባኝ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ወይም ከተሰጠ በኋላ የአፈፃፀም እርምጃ ከመቀጠሉ በፊት ቀረጡን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 50% (ሃምሳ በመቶ) ይነሳለታል።

ረ. በሁለተኛ ይግባኝ ውሣኔ መሠረት የአፈፃፀም ፋይል ተከፍቶ ከአፈፃፀሙ ትዕዛዝ በፊት ቀረጡን አጠናቆ የከፈለ እንደሆነ የመቀጫው 40%(አርባ በመቶ) ይነሳለታል።

## አንቀጽ 7. <u>መቀጫዎች ሙሉ በሙሉ የሚነሱባቸው ልዩ ሁኔታዎች</u>

1. በዚህ መመሪያ መሠረት መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል የሚነሳበት ሁኔታ በአንቀጽ 5 እና 6 መሠረት የተመለከተ ቢሆንም ግብር ከፋዩ ፍሬግብሩን፣ ታክሱን፣ ቀረጡን ወይም መቀጫውን እንዳይከፍል ያደረገው/ያደረጉት፡-

   ሀ. ድንገት ደራሽ ችግር ማለትም ድርቅ፣ ተምች፣ የእንስሳት ወረርሽኝ በሽታ፣ መብረቅ፣ ማዕበል፣ ይህን የመሳሰለት የተፈጥሮ መቅሰፍቶች፤

   ለ. የውጭና የአገር ውስጥ ጦርነት፤

   ሐ. የግብር ከፋዩ መሞት፣ ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ሕመም ሲያጋጥም፤

   መ. ድርጅቱ በኪሳራ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ሲዘጋ፤



Records and Documentation Section

ሠ. የሥራ ግብር እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸው ተቀጣሪዎች ከሥራ ሲቀነሱና ሌላ የገቢ ምንጭ የሌላቸው፤

ሆነው ሲገኙ የተጣሉት መቀጫዎች ሙሉ በሙሉ እንዲነሱ ይደረጋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት ሁኔታዎች በመከሰታቸው ምክንያት መቀጫን ስለማንሳት የሚቀርበው አቤቱታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ታይቶ በሚቀርበው የውሣኔ ሃሳብ መሠረት ውሣኔ የሚሰጠው በታክስ ባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም እንደ ሁኔታው በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል።

# ክፍል ሦስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 8 መቀጫዎች የማይነሱባቸው ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣6 እና 7 በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫዎች እንደሚነሱ የተመለከተ ቢሆንም፦

1. ግብር/ታክስ ቀረጥ ከፋዩ ስለገቢው ምንጭ ወይም መጠን ስለሥራው መጠን ወይም ግብር/ታክስ ቀረጥ ለመወሰን የሚያስፈልጉ መግለጫዎችን ወይም ሠነዶችን ለማቅረብ እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ፤

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ/መግለጫ በማቅረብ የታክስ ባለሥልጣኑን ውሣኔ ለማዛባት የሞከረ ወይም እንዲሳሳት ያደረገ እንደሆነ እና በዚህም ምክንያት በወንጀል የተከሰሰና የተፈረደበት እንደሆነ፤

3. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 91 በተመለከተው መሠረት ግብር ከፋዩ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ባለማቅረቡ የተጣሉት መቀጫዎች፤

4. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 33/1/ እንደተደነገገው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ከተመዘገበ ሰው የገዛ ማናቸውም ሰው

Ministry of Revenue
Records and Documentation Section

በፈፀመው የማጭበርበር ተግባር ወይም ያልሆነውን እንደሆነ አድርጐ በመቅረቡ ምክንያት የተመዘገበው ሰው በስህተት ግብይቱ ከታክስ ነፃ ወይም በዜሮ የማስከፈያ ልክ እንደሚከፈልበት አድርጐ የወሰደ እንደሆነና የታክሱ ባለሥልጣን ወለድና መቀጫውን ጨምሮ ያልተከፈለውን ታክስ ከገዢው ጠይቆ ሲያስከፍል፤

5. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 45/ለ/ እንደተደነገገው ተከፋይ የሚሆነው ታክስ እንዲቀንስ ወይም የሚፈቀደው ተቀናሽ እንዲጨምር የሚያደርግ ሀሰተኛ የሆነ የታክስ ደረሰኝ አዘጋጅቶ ያቀረበ ወይም የታክስ ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠና ወይም ታክሱንም ያልሰበሰበ ወይም የሰበሰበ መሆኑ ሲደረስበት፤

6. ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው የታክስ ደረሰኝ በመስጠት ታክስ የሰበሰበ እንደሆነ፤

7. በአዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 47፣በአዋጅ ቁ.307/95 አንቀጽ 21 እና በአዋጅ ቁ. 308/95 አንቀጽ 24 በወለድ መልክ፤

የተጣሉት አስተዳደራዊ መቀጫዎች አይነሱም::

## አንቀጽ 9 የውክልና ሥልጣን

በፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ውስጥ በባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በገቢዎች ሚኒስትር በሚሰየሙ አባላት የሚቋቋመው የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት የቴምብር ቀረጥ ክፍያ ግዴታን ባለመወጣት የሚጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎችን በሚመለከት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለማየትና የውሣኔ ሃሳብ ለታክስ ባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ለማቅረብ የውክልና ሥልጣን ተሰጥቶታል::

## አንቀጽ 10 መመሪያው የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ________ቀን 1996 ዓ.ም.

Ministry of Revenues
Records and Documentation Section

05 ሚያዝ 1996